# ኢትዮጵያ የአውራ ፓርቲ ወይስ
# የአሃዳዊ ፓርቲ መገለጫ ስርዓት?

( ክፍል አንድ)

ከፀሐዬ ደባልቀው
ዋሽንግተን ዲ.ሲ.
February 17, 2012

የታሪክ ተመራማሪዎችና የፖለቲካ ጠበብት እንዲሁም የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትንታኔ በሳል ምሁራን የአውራ ፓርቲና የአሃዳዊ ፓርቲ መገለጫን ተንተርሶ ሰፊ ውይይትና ሙግት እንዲያም ሲል ጥልቅ እሰጥ አገባ ሲለዋወጡ መዝለቃቸው አያሌ የብራናና የወረቀት መረጃዎችን መጠቃቀስ ብቻ ሳይሆን ዘመን አመጣሹ የድረ-ገጽ የድምጽ እና የምስል መረጃዎችንም ዋቢ ማድረግ ይቻላል::

ይልቁንም ይኸንን በምሁራን አካባቢ የተስተዋለውን እሰጥ አገባ ወደ ሃገራችን የቅርብ ታሪክ ስንመልሰው ፍንትውና ኩልል ብሎ የሚታይ ክስተትን ይዞ ብቅ ማለቱን ይመለከቷል::

በተለይም በኢትዮጵያችን በ2010 የተካሄደው አራተኛውን ሃገራዊ ምርጫን ተከትሎ በተፈጠረው ቁልጭ ያለና ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የአብዛኛውን መራጭ ድምፅ ይሁንታን ተገን በማድረግ በትረ ስልጣኑን መቆጣጠሩ እውን ከሆነበት ማግስት ጀምሮ የሀገራችንን የፖለቲካ ሕዋ እጣ ፈንታ በእጅጉ የሚወስነው መንታ መንገድ ለይቶለታል ኢትዮጵያም በአሃዳዊ ፓርቲ ስልጣን መዳፍ ስር ወድቃለች የሚል በጥድፊያ ላይ የተንደረከከ ፖለቲካዊ ህፀፅ እንደ መደምደሚያ መወሰዱ ጉዳዮን ይበልጥ አነጋጋሪ እንዲሆን በር ከፍቷል::

ጉዳዩ ለክርክር በር መክፈቱ ባልከፋ ነበር ለክርክሩ ራሳቸውን በአንድ ወገን ያቀረቡት ወገኖች እጅ በመጠንቆል የገፉበት ጉዳይ ቢኖር ክስተቱ በኢትዮጵያችን ከአሁን በፊት የታየና አምባገነናዊ ስርዓትን ለመውለዱ አንድና ሁለት የማይባልለት ተጨባጭ ማስረጃ ነው ሲሉም ኢህአዴግን ወደ አሃዳዊ የፓርቲ አገዛዝ ያሸጋገረ ምዕራፍ ነው ሲሉና በአጽንኦት ሲከራከሩ ተደምጧል::

ይሁንና ክርክሩ መግጠሙ ላይ ሳይሆን ቁምነገሩ ያለው ክርክሩ ምን ያህል ከእውነታ ጋር ይዛመዳል? ምን ያህልስ ከዓለም አቀፉ ተሞክሮ ጋር ይጎዳኛል? በማለት ውሃ ለመቋጠሩ አስረጂ ፍለጋ ብዙ ርቀት አለማስኬዱ ነበር፡፡

እንግዲህ ከዚህ እሰጥ አገባ ትይዩ የታሪክ ማስረጃንና የተጨባጭ ፖለቲካዊ የዕለት ተዕለት ተሞክሮን ዋቢ ማድረግን የግድ ይላል፡፡

<u>በሀገራችን እንጀምር፤</u>

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊት ዲሞራሲያዊት ሀገር ከመሆኗም በላይ ሕገ መንግስታዊ የፖለቲካ ሥርዓት የሰፈነባትና የሕዝቦቿ የመደራጀት መብት፣ የሰብአዊ መብት፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ እና የመፃፍ መሰረታዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲሁም ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መብቶች በሕገ መንግስት ልዕልና ሥር የሕግ እውቅናና የህግ ጥበቃ ለመጐናጸፍ የቻሉበት ሥርዓት የሰፈነባት ሀገር ናት፡፡ በዚህ ፖለቲካዊ ምህዳር ውስጥ ሊሰርጽና ሊመነጭ የሚችለው ልዩ ልዩ የፖለቲካ እምነት ባላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና አደረጃጀቶች ዙሪያ በሚደረግ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ውድድር በአሸናፊነት የብዙሃኑን መራጭ ሕብረተሰብ ድምፅ በማግኘት ብቅ የሚሉና በየወቅቱ በሚከሰት የፖለቲካዊ ቀመር ነፀብራቅ የሆነ ሥርዓት ዓይነተኛ መገለጫው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ይኸ አባባል በተጨባጭ የሃገራችን የፖለቲካ ህላዌ መስፈርት አኳያ ሲዳሰስ ኢትዮጵያችን በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ አግባብ የፖለቲካ ዕምነቶቻቸውን ለማስረፅ ውድድር ውስጥ የገቡ አያሌ የፖለቲካ ፓርቲዎች ደሴት መሆኗን ያምኗል፡፡

ከነዚህ አያሌ የፖለቲካ አደረጃጀቶች አንዱ ወይም በጥምረት ሕጋዊ፣ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ አኳኋን የመራጭ ሕዝቡን ይሁንታ በመቀዳጀት የፖለቲካ መዘውሩን መቆጣጠር ይችላል፡፡ ከዚህ አባባል ብዙ እሩቅ ሳንጓዝ ከሰባት ዓመታት በፊት በሀገራችን የታየውን የፖለቲካ ውድድር ውጤት መቃኘቱ በቂ ይሆናል፡፡

ይኸውም ኢህአዴግና ቅንጅት በአንዳንዱ የምርጫ ቦታ ላይ መሳ ለመሳ የመራጩን ሕዝብ ድምፅ የተጋሩበት በአንዳንዶቹ ደግሞ አንዱ ወይም ሌላው ፓርቲ አብዝሃ ድምፅ ያገኙበት ክስተት ተፈጥሮ ነበር፡፡

ይሁንናም ይህ ህገ መንግስቱ የፈጠረው የሰላማዊ የህጋዊና የዲሞክራሲያዊ መንገድ ውልድ የነበረው ሂደት በቅንጅት በትረ ስልጣኑን በሕገ ወጥ መንገድ ጠቅልሎ የመውሰድ አባዜ ሊጨናገፍ ችሏል፡፡

ቀጥሎ በተካሄደው የ2010 ብሄራዊ ምርጫ ያለፈውን ድክመቱን ከሕብረተሰቡ ጋር በግልፅ በመወያየት ሕፀፁን ተቀብሎ ለማረምና ለማስተካከል ራሱን ያዘጋጀው ኢህአዴግ የመራጩን ሕብረተሰብ ይሁንታ በማግኘት ስልጣኑን ሲቆጣጠር በሃገራችን አዲስ የፖለቲካ ክስተት ብቅ ያለው ኢህአዴግ በአውራ ፓርቲነት ግማሽ ርቀት ላይ የሚገኝበትን የአሁኑን የአምስት ዓመት የፖለቲካ ስልጣን ዘመኑን በአደራነት የተረከበበት ጊዜ ነበር፡፡

እንግዲህ አንድ ስርዓት በአውራ የፖለቲካ ድርጅት ሊመራ ይችላል ሲባል መሰረታዊ መደላድሉ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚመጣው፣

1ኛ ያ ስርዓት ሕገ መነግስታዊ መሆኑን፣

2ኛ ሕገ መንግስቱ ስልጣን በዲሞክራሲያዊ፣ በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ ብቻ መያዝ የሚቻል መሆኑን በግልፅ የደነገገ እንደሆነና፣

3ኛ ይኸንኑ ድንጋጌን ተከትሎ መሬት ላይ ተፎካክሪና ተወዳዳሪ የሆኑትና በሰላማዊ፣ በሕጋዊና በዲሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ ዓላማቸውን የሚያራምዱ አያሌ ፓርቲዎች ከሃገር አቀፍ ጀምሮ በተዋረድ ሕልውናቸው ሲረጋገጥና በተግባር ሲንቀሳቀሱ የሚታዩበት ሁኔታ መኖሩን እና መራጩ ሕዝብም ያለምንም ጫና ፖለቲካዊ መብቱን ሲያረጋግጥ ማየቱ የግድ ይላል፡፡

ከዚህ አኳያ ዛሬ በሀገራችን በኢትዮጵያ ከማዕከል እስከ ክልል በሀገር አቀፍና ከዚያም በመለስ በሰላማዊና በዲሞራሲያዊ አግባብ የፖለቲካ ዕምነታቸውን ለህዝቡ በማቅረብ የመራጩን ሕብረተሰብ ይሁንታን በመሸመት በየእርከኑ ለስልጣን አውራውን ኢህአዴግን የሚፎካከሩ ወደ አንድ መቶ የሚሆኑ በህጋዊ መንገድ የተመዘገቡ የፖለቲካ ድርጅቶች በመላው ሀገሪቱ ይናኛሉ፡፡

ከዚህ መነጽር ትይዩ በሀገራችን በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ያለው የፖለቲካ ስዕል የሚያመለክተው ሁሉንም መመዘኛዎች ያሟላ የፖለቲካ ስርዓት መሆኑን ነው፡፡

ይቀጥላል